# የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሥነምግባር ደንብና በደንቡ ማስፈፀሚያ መመሪያ ላይ ባደረጉት ድርድር ስምምነት የተደረሰበት ሰነድ

## መግቢያ

እኛ በሀገራችን ግል፣ ነፃ፣ ፍትሃዊና በሕዝብ ተቀባይነት ያለው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የተስማማን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣

1. በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ መሆን ለሰለጠነ፣ ሕጋዊ፣ ዴሞክራሲያዊÂ ሰላማዊ ትግልና ውድድር ያለውን ፋይዳ በማመንና በመቀበል፣

2. በኢትዮጵያ በመገንባት ላይ ባለው yዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚያስማሙን ጉዳዮች በጋራ እየሠራን በልዩነታችን ደግሞ ሰላማዊና የሰለጠነ ትግል በማካሄድና የሕዝብ ውሣኔ ተቀብለን በመጓዝ የሀገር ግንባታ ኃላፊነታችንን መወጣት እንዳለብን በመስማማት፣

3. የወደፊት ግንኙነታችን በግል በመነጋገር፣ በቅንነት፣ በመቻቻል እና ሰጥቶ በመቀበል መርህ እየተመራ በሀገራችን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እና ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብቱ የበኩላችን የማይተካ ሚና እንዳለን በመገንዘብ፣

4. ባለፉት ሦስት ዙሮች ከተካሄዱት ሀገር አቀፍ ምርጫዎች ትምህርት በመውሰድ አራተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫም ሆነ ወደፊት በሀገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ሁሉ በላቀ ደረጃ ግል፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ# በህዝብ ተቀባይነት ያላቸውና ሰላማዊ ሆነው መካሄድ እንዳለባቸው በመስማማት፣

5. የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ዓለም አቀፍ ደረጃ በጠበቀ የፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር የተመራ የምርጫ ዘመቻና ውድድር ማካሄዳቸው አስፈላጊ መሆኑን እና ይህን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በየደረጃው የጋራ ምክር ቤቶች ማቋቋማችን ከፍተኛ ሕዝባዊ ጠቀሜታ እንዳለው በመገንዘብ፣

6. በሀገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ሁሉም ብሔረሰቦች እና በአጠቃላይ የሀገራችን ዜጎች በእኩልነት፣ በፍቅርና በአንድነት ለመኖር ያላቸው ፍላጎትና የሉዓላዊነታቸው መገለጫ በመሆናቸው በዚህ የሥነ-ምግባር ደንብና በሌሎች ምርጫ ነክ ህጎች መሠረት የተካሄዱ ምርጫዎች ትክክለኛ ሂደትና ውጤት በፀጋ ለመቀበል ያለንን ቁርጠኝነት በማረጋገጥ፣

7. የህዝባችንን ውሳኔ በመፃረር የመንግሥት ስልጣን ላይ ለመቆየትም ሆነ ከህገ-መግሥታዊ ሥርዓት ውጪ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ የሚደረጉ ማናቸውንም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ እንቅስቃሴዎች የማንቀበል መሆናችንን በማረጋገጥ፣

8. የምርጫ ቦርድና የፍትሕ አካላት ማለትም ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግና የዳኝነት ሥርዓቱ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነትና በገለልተኛነት ሕዝባችንን ማገልገል እንዳለባቸው በመስማማት እና የአካባቢ መስተዳድር አካላት የሚሠጡት መንግሥታዊ አገልግሎት ያለአድልዎ መሰጠት እንዳለበት እና ለተፈፃሚነቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ማበርከት ያለባቸውን የጋራ ሃላፊነት በመገንዘብ በጋራ ለመሥራት በመስማማት፣

9. በህግ ተመዝግበው የሚገኙና በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ውድድር ወደ ስልጣን ለመምጣት በሚሹ ፓርቲዎች መካከል የሚካሄደው ውድድር ከጥላቻና አለመተማመን በፀዳ፣ ጤናማ ግንኙነት መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብና |ተግባራዊntÜ አንአት በመስጠት፣

10. እኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል፣ ተጠባባቂ ጦር እና የአካባቢ ታጣቂ ኃይል የሀገራችንን ህዝብ አንድነት ከወራሪ ኃይል ለመጠበቅ እና የሀገራችን ዳር ድንበር ለማስከበር የተደራጁ ኃይሎች መሆናቸውን በመገንዘብ

ሠራዊቱ በህገ-መንግሥቱ መሠረት ተግባሩን ከፖለቲካ ፓርቲዎች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን እንዲያከናውን የተደነገገ መሆኑን በማክበር፣

11. የፕሬስ ነፃነት ለሰብዓዊ መብት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት እና ለአንድ ሕዝብ ሁለንተናዊ ዕድገት ያለውን ልዩ አስተዋጽኦ በመገንዘብ፣ ለተፈፃሚነቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ መቆም ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ፣

12. ማንኛውም ለምርጫ አገልግሎት ሊውል የሚችል በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኝ የሕዝብ ሀብትና ንብረት ለሁሉም ፓርቲዎች በእኩልነትና ያለአድልዎ አገልግሎት እንዲሰጥ እንዲሁም ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጎማ በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስምምነት መሰረት ለሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች መከፋፈል እንዳለበት ዳግመኛ በመግለጽ፣ ⊢ተግባራዊntÜም የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ለመሥራት በመስማማት፣

13. የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሳለፈው የረጅም ጊዜ የመንግሥት ሥርዓት ሲታገልለት የኖረውን የሕዝብ ሥልጣን አመንጭነት፣ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት መብት አጠናክሮ ለማስቀጠል እኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት ያለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ዳግመኛ በመገንዘብ እና ለተፈፃሚነቱ ያለንን ቁርጠኛ ፍላጎት በማረጋገጥ፣

14. መላው የኢትዮጵያ ሕዝባችን እና የተለያዩ መንግሥታዊና የፖለቲካ ድርጅቶች አካላት፣ በሀገራችን የዲሞክራሲ፣ የሰብዓዊ መብትና የሕግ የበላይነት መጎልበት አስፈላጊነትና በተለይ የምርጫ 2002 ዓ.ም. ሂደትና ውጤት ስኬታማ መሆን በእነርሱ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ለማድረግ ተገቢው ተከታታይ ትምህርት እና ሥልጠና ለመሰጠት ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለብን በመገንዘብ እና ለተፈፃሚነቱም ያለንን የጋራ ቁርጠኝነት በማረጋገጥ፣

15. የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞችን ጨምሮ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ለማረጋገጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ወይም እንቅፋት

እንዳይደረግበት ያለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ዝግጁነታችንን በድጋሚ በመግለፅ፣

16. እኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባላት በፖለቲካ ተፅኖ ምክንያት በተለያዩ ጊዜያትና የሀገሪቱ ክልሎች በአባሎቻችንና በደጋፊዎቻችን ላይ ይደርሱብናል በማለት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸውን ችግሮች በዚህ የስነምግባር ደንብና የማስፈፀሚያ ሰነድ መንፈስ በመመርመር ተጨባጭ ሆነው ከተገኙ ለማስተካከል ያለንን የጋራ ቁርጠኝነት በማረጋገጥ፣

17. እኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት አባላት የምርጫ ቦርድ አሠራርን፣ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞችን በተመለከተ በሚነሱ የተለያዩ ቅሬታዎች ዙሪያ አሉ የሚባሉ ችግሮች ተጣርተው ተጨባጭ ሆነው ከተገኙ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ ነፃና ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ ያለውን የላቀ አስተዋጽዖ በመገንዘብ በጋራ መቆማችንን በማረጋገጥ፣

18. ሦስቱ የመንግስት አካላት ማለትም ህግ አውጭው፣ ህግ አስፈፃሚውና የዳኝነት አካላት የግልጽነት፣ የታማኝነትና የተጠያቂነት ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው የተቀበሉና ተግባራዊntÜNም ለማክበር እና ለማስከበር ቃል የገቡ መሆናቸውን በማጤን እኛም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባላት ለተፈፃሚነቱ በጋራ የቆምን መሆናችንን በማረጋገጥ፣

19. ከነዚህ መርሆዎች በመነሳት ዓለም አቀፍ የዴሞክራሲና የምርጫ ድጋፍ ሰጪ ተቋም /International Institute for Democracy and Electoral Assistance IDEA/ በመባል የሚታወቀው ድርጅት ያዘጋጀውን የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነምግባር ደንብ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ተርጉሞ ያቀረበውን እንደመነሻ በመውሰድና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የደቡብ አፍሪካንና የጋናን ልምድ ጨምሮ በሀገራችን ሁኔታ መካተት አለባቸው ብሎ ያዘጋጀውን ሰነድ በተጨማሪነት በማገናዘብና እንዲሁም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) እና ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ

ፓርቲ (ቅንጅት) በድርድሩ ወቅት ያነሷቸውን ሀሳቦች በቂ ጊዜ ወስደን በመመካከር አስፈላጊ ማሻሻያዎች አድርገን በመቀበል፣

20. የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንቡ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ስልት በምክክር በማዘጋጀትና ተስማምተን በመቀበል ተፈፃሚነቱን የሚያረጋግጡ የጋራ ምክር ቤቶች በየደረጃው ለመመስረት በመስማማት፣

ከዚህ ቀጥሎ በሁለት ሰነዶች ማለትም "የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ" እና "የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብን በሥራ ላይ ለማዋል የተዘጋጀ መመሪያ" በሚል አዘጋጅተን የተስማማንÆcWN ሰነዶች በማዋሃድ የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አካል ሆነው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት በአዋጅ መልክ እንዲደነገጉ በመስማማት ሰነዶቹን መቀበላችንንና በሥራ ላይ እንዲውሉ መስማማታችንን በፊርማችን አረጋግጠናል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር
(ኢህአዴግ)

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
(መኢአድ)

____________________________________

____________________________________

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ

(ኢዴፓ)

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

(ቅንጅት)

____________________________________

____________________________________

# የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ

**አንቀጽ 1** <u>ስለ ሥነ ምግባር ደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን</u>

በዚህ የስነምግባር ደንብ "የፖለቲካ ፓርቲ"፡-

1. ማንኛውም በዚህ የስነምግባር ደንብ ለመመራት የተቀበለ አካል ማለትም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች፣ እና ፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት ወይም ጥምረት ወይም ንቅናቄ እና
2. ማንኛውም በዚህ የስነምግባር ደንብ ለመመራት የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት፣ ወኪሎች እና ተጠሪዎች፤

ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 2** <u>ስለ ሥነ ምግባር ደንቡ መርሆዎች (principles of the code)</u>

1. የአንድ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ስርዓት የሚመረጥ መንግስት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ይመሠረታል፡፡

   ሀ. መራጩ ህዝብ በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለእጩዎች ባህሪ የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሲያደርጉ እንደሆነ እና

   ለ. መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለ ፍርሃት፣ ያለ ተፅእኖ ወይም ያለጫና ወይም ከጉቦ ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት ሲችሉ ነው፡፡

2. ይህንን የሥነ ምግባር ደንብ የተቀበሉ ፓርቲዎች ሁሉ በቅን ልቦና እና በፈቃደኝነት እየተመሩ፡-

   ሀ. እነዚህ የስነምግባር ደንብ መርሆዎች እንዲከበሩ፣

   ለ. ምርጫው የመላው ህዝብ ነፃ እና ተቀባይነት ያለው ውሳኔ መግለጫ ሆኖ እንዲታወቅ፣

   ሐ. የመራጩ ህዝብ ውሳኔ በሁሉም የተከበረ እንዲሆን፣

3. ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መመሪያዎች ጋር በተጣጣመ አኳኋን ይንቀሳቀሳሉ፡፡

## አንቀጽ 3 <u>ለደንቡ ተገዢ ስለ መሆን</u>

1. ይህን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ፡-

   ሀ. በዚህ የስነምግባር ደንብ ተገዝቶ ይንቀሳቀሳል፣

   ለ. መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ እና አባላቱ ይህንን የስነምግባር ደንብ እንዳይጥሱ ቁርጠኛ እርምጃ ይወስዳል፡፡

   ሐ. የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎችና አባላት ይህንን ደንብ የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጽሙ የተከለከሉ ድርጊቶች ደጋፊዎችም ከመፈጸም እንዲቆጠቡ የሚያደርግ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

   መ. ይህ ደንብ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ እያቀረበ ቅሬታ የማሰማት መብቱን አለአግባብ መጠቀም የለበትም፡፡

2. ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተስማማ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች እጩዎች አባላት እና ደጋፊዎች፡-

   ሀ. ይህንን የስነምግባር ደንብ እንዲያከብሩ ያደርጋል

   ለ. የስነምግባር ደንብ እንዲከበር ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል

**አንቀጽ 4** **<u>ህግን ስለ ማክበር</u>**

ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ ይህንን የምርጫ ስነምግባር ደንብ አካቶ የዳበረውን የምርጫ ህግ፣ ደንብ እና መመሪያ ያከብራል፡፡

**አንቀጽ 5** **<u>ስለ ምርጫ ዘመቻ አካሄድ (Campaign Management)</u>**

1. ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

   ሀ. ሁሉንም ሌሎች የፓለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ መብትና ነፃነት እንዲሁም የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለስጋት የማሰራጨት መብት ያከብራል፣

   ለ. እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌላውን የህብረተሰብ ክፍል መብት ያከበረ ይሆናል፣

   ሐ. የፕሬስ ነፃነት ያከብራል፣

   መ. ድርጅቱ ያሉትን ጽህፈት ቤቶች ሁሉ በመጠቀም፣ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ህዝብ ያላቸውን አግባብነት ያለው ተደራሽነት ለማረጋገጥ ይጥራል፣

   ሠ. ተዛማጅ በሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚሹ መራጭ የመሆን እድል ያላቸው ዜጎች ሁሉ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ያስችላል።

2. ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

   ሀ. ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ አያዋክብም ወይም እንቅፋት አይፈጥርም፣ እንዲሁም የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጎል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ ወይም እንዲዳከም አያደርግም፣

ለ. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያዎች፣ በራሪ ፅሁፎች እና ፖስተሮች እንዳይሰራጩ አያውክም፣

ሐ. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተር አያበላሽም ወይም አያጠፋም፣

መ. ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ሰፊ ሕዝባዊ ድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባዎች ወይም የእግር ጉዞና ሰላማዊ ሰልፎች እንዳያደርግ አያግድም፡፡

ሠ. ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ አይከለከልም፡፡

ረ. ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ አይፈቅድም፡፡

**አንቀጽ 6.** <u>**ስለምርጫው ሂደት**</u>

1. ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ. ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር በመተባበር

i. ድምጽ የመስጠት ሂደቱ ሰላማዊ እና ስነስርዓቱ የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፤

ii. መራጮች ያላቸውን የመምረጥ መብት ከሚያበሳጭና ከሚያደናቅፉ ሁኔታዎች በፀዳ፣ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲያደርጉ

ይሠራል፡፡

ለ. ከድምጽ መስጫ በፊት፣ በድምጽ መስጫ ጊዜና ከድምጽ መስጫ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች ፀጥታና ደህንነት ያረጋግጣል፡፡

ሐ. የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች እና ኃላፊዎች ያከብራል፤ ይተባበራል፣

መ. የድምፅ አሰጣጡን ሚስጢራዊነት ያከብራል፤ እንዲከበር ያግዛል፣

ሠ. ይህንን ደንብ ያከብራል፣ ለመራጩ ህዝብ ያስተዋውቃል፣ ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹና ለእጩዎቹ ያስተምራል፡፡

2. ይህንን ደንብ የተቀበለ ፓርቲ፡-

ሀ. የድምጽ መስጫ ጣቢያን በኃይል በመቆጣጠር ወይም በሌላ በማንኛውም ህገወጥ መንገድ ተጠቅሞ ድምፅ ለማግኘት አይንቀሳቀስም፣

ለ. ያለአግባብ ወይም ከቅን ልቡና ውጪ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ተግባራት ፣ የድምፅ አሰጣጥ ወይም የድምፅ ቆጠራ ሂደት አያውክም፣ ጣልቃ አይገባም፣

ሐ. የድምፅ አሰጣጡ ሚስጥራዊ እንደማይሆን ለመራጮች የሀሰት መረጃ አይሰጥም።

**አንቀጽ 7** **ፍትሃዊና ነፃ ምርጫ ውጤት ስለመቀበል**

ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፣-

1. በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠን የምርጫ ውጤት ይቀበላል፣
2. ያለውን ማንኛውንም ቅሬታ ለሚመለከታቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ወይም የምርጫ ቦርድ ወይም ለፍርድ ቤቶች ብቻ ያቀርባል፣
3. ከላይ የተመለከቱት ውዝግብ ፈቺ አካላት የሰጡት የመጨረሻ ውሳኔ ይቀበላል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 8** **ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል ቋንቋ** (language)

1. ይህን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

   ሀ. የምረጡኝ ዘመቻውን ሲያደራጅና ሲያካሂድ ለአጠቃላይ የምረጡኝ ዘመቻ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ እና ለድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና ምቹነት አስተዋፅኦ በሚያደርግ አኳኋን ይሆናል፣

ለ. ፓርቲው ከሚጣልበት ኃላፊነትና ካለው ክብር ጋር በተመጣጠነ ደረጃ ይንቀሳቀሳል።

2. ማንኛውም ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ንግግር የሚያደርግ ሰው፡-

ሀ. ግጭት ቆስቋሽ ወይም ስም አጥፊ ንግግር ያስወግዳል፣

ለ. በማንኛውም መልኩ በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ አመጽ የሚጋብዝና ስጋት የሚፈጥር ንግግር ያስወግዳል፡፡

3. ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ በይፋም ሆነ በስውር አመፅ የሚቀሰቅስ ወይም የሚያስፈራራ የቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔቶች ወይም ፖስተር አያወጣም፡፡

## አንቀጽ 9 <u>ስለምልክቶች (symbols)</u>

ማንኛውም ይህን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1. የሌሎች ፓርቲዎች ሎጎ ወይም የምርጫ ምልክት አይቀዳም ወይም አስመስሎ አይጠቀምም፣
2. የሌሎች ፓርቲዎች የፖለቲካ ወይም የምርጫ ቁሳቁስ አይሰርቅም፣ አያበላሽም፣ አያጠፋም ወይም
3. ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከለ ማንኛውንም ተግባር እንዲፈፅሙ አይፈቅድም፡፡

## አንቀጽ 10 <u>ስለማስፈራራት እና አመጽ ስለመቀስቀስ (intimidation and violence)</u>

ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1. ማንኛውም አይነት ማስፈራራት ወይም ወከባ የተከለከለ መሆኑን ተቀብሎ፡-

ሀ. የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩ ተወዳዳሪዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ማንኛውንም ሰው በየትኛውም ጊዜ ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልፅ የሚከለክሉ መመሪያዎች ያወጣል፡፡

ለ. አመፅ ወይም አመፅን መጋበዝ በመቃወም ያስተምራል፣ በተጨማሪም በኃላፊዎቹ፣ በእጩዎቹ፣ በአባላቱ ወይም

በደጋፊዎቹ የሚፈፀሙ ስጋቶችና ውድመቶች ወይም የህዝብ ሰላም የሚያናጉ ድርጊቶች ወይም ወደነዚህ የሚያመሩ ዛቻዎች በመቃወም ያስተምራል፣

ሐ. ሌሎች ሰዎች እና ፓርቲዎች እንዲሁም ንብረታቸውን ያከብራል፡፡

2. ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ማንኛውንም ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሳሪያ መሳሪያዎች በመያዝ ወደ ፖለቲካ የድጋፍ ሰልፎች፣ (political rally) ስብሰባዎች፣ የእግር ጉዞዎች ወይም ሰላማዊ ሰልፎች ይዘው እንዳይመጡ ያስተምራል፡፡

3. ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ. የፓርቲውን ጥንካሬ ለማሳየት ወይም የበላይነቱን ለማረጋገጥ ሲል በማንኛውም የሁከት ወይም የአመፅ (violence) እንቅስቃሴ አይሳተፍም ወይም እንዲደረግ አይፈቅድም፣

ለ. በህዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ ውድመት (damage) እንዳይደርስ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ይከለከላል፣

ሐ. ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተደነገጉ ማናቸውንም ክልከላዎች እንዲፈፅሙ አይፈቅድም፡፡

**አንቀጽ 11** <u>ስልጣንን ያለአግባብ ስለ መጠቀም (abuse of position)</u>

1. ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ. ያለውን የሥልጣን ኃላፊነትና የተለየ ዕድል ወይም ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ለፖለቲካ ፍላጎቱ ለመጠቀም መደለያ ማቅረብን፣ ቅጣትንና ማንኛውንም የማስፈራራት መንገድ አይጠቀም፣

ለ. የፌዴራል መንግስት፣ የክልል መንግሥት፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤትን ወይም ሌላ የህዝብ ሀብት በምርጫ ህጉ ከተፈቀደው አኳኋን ውጭ ለምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ አይጠቀምም፡፡

2. በዚህ ክፍል ውስጥ "ስልጣን፣ ልዩ መብት ወይም ጫና ማለት የወላጅ፣ የዝምድና፣ የመንግስት፣ የፖሊስ፣ የአካባቢ ታጣቂ ኃይል፣ የወታደራዊ ወይም ልማዳዊ /ባህላዊ/ ስልጣን" ያካትታል፡፡

## አንቀጽ 12 <u>ስለ ሙስና ተግባር (corrupt practice)</u>

ይህንን የስነምግባር ደንብ የተቀበለ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1. ኃይል በመጠቀም (coerce) ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ (inducement) በመስጠት መራጩ ህዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ድምፁን ከመስጠት እንዲታቀብ አያደርግም፣
2. ኃይል በመጠቀም (coerce) ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ (inducement) በመስጠት ሰዎች እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነታቸው እንዲወጡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዳይወጡ አያደርግም፣
3. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በሚመራው ወይም በሚሠራበት ተቋም አግባብ ያልሆነ ድጋፍ ወይም እርዳታ በመጠቀም እጩ ተወዳዳሪን አያስተዋውቅም ወይም የሌሎች ተወዳዳሪዎች የማስተዋወቅ ዕድል አያደናቅፍም፡፡

## አንቀጽ 13 <u>ቀጣይ ግንኙነት ስለ መፍጠር (continued communication)</u>

1. ይህንን ደንብ የተቀበለ ፓርቲ ደንቡን አክብረው ለመንቀሳቀስ ከተስማሙ ሌሎች ፓርቲዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ፈጥሮ ይንቀሳቀሳል፣
2. በምርጫ ህጉ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ዘመቻ ወቅት እና በማናቸውም ጊዜ የጋራ ጉዳይ በሆኑ ነጥቦች ላይ የመወያያ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል ምክር ቤት ይህንን ደንብ በተቀበሉ ፖለቲካ ፓርቲዎች ይመሠረታል፡፡ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላት ተወካዮች ይይዛል፣

ሀ በፌዴራል ደረጃ ለምርጫ ውድድር ተመዝግበው የፖለቲካ ፓርቲዎች ስነ-ምግባር ደንብ ባወጡትና በተፈራረሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣

ለ. በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደግሞ በየደረጃው የምርጫ ተወዳዳሪ በሆኑ ፓርቲዎች አባላት፣

ሐ. የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት በታዛቢነት መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እነሱ ችግር በገጠማቸው ጊዜ ለምክር ቤቱ ጥያቄአቸውን አቅርበው በዚህ ደንብ መሰረት ያስወስናሉ፣

መ. የምርጫ አስፈፃሚዎች በፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት የድርድሩ ውይይት ላይ አይገኙም፣ ሆኖም የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ እንዲገኙ ከወሰነ ያለድምጽ ስብሰባ ላይ መገኘት ይችላሉ፡፡

# የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የተዘጋጀ መመሪያ

## ምዕራፍ I. የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስለመመስረት

1.1 በምርጫ ሥነ ምግባር ደንቡ ላይ ተስማምተው የተፈራረሙት ፓርቲዎች ደንቡን ተግባራዊ ለማድረግና በምርጫው ሂደት በሚነሱ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም እና ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት በኢትዮጵያ በሚጎለብትበት ጉዳዮች ላይ በመመካከር ችግሮችን እያቃለሉ ለመጓዝ ይችሉ ዘንድ በደንቡ የሰፈረውን ቋሚ የግንኙነት ሥርዓት በማበጀት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት መስርተዋል፡፡ ለተመሳሳይ ዓላማ

እስከ ምርጫ ክልል ድረስ የፓርቲዎች የጋራ ም/ቤቶች እንዲቋቋሙ ተስማምተዋል፡፡

## 1.2 የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ዓላማ፡-

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1.2.1 በሀገራችን በ2002 ዓ.ም እና ወደፊት የሚካሄዱ ምርጫዎች ግልፅ፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ተአማኒና ሰላማዊ እንዲሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት አለም አቀፍ የስነ ምግባር ደረጃ ባሟላ መልኩ እየተመሩ ለማስፈፀም የጋራ አካል ሆኖ ማገልገል፣

1.2.2 በምርጫ አፈፃፀም ሂደትና ውጤት፣ ባጠቃላይ በፖለቲካ ፓርቲዎች ግንኙነት የሚከሰቱ ችግሮች የስነ ምግባር ደንቡን ያካተተ የምርጫ ህግ ተከትሎ በጋራ ውይይትና መግባባት ለመፍታት የሚያስችል የውይይት፣ የምክክርና የቁጥጥር አካል ሆኖ ማገልገል፡፡

## 1.3 የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አመሰራረት

### 1.3.1 አገር አቀፍ አደረጃጀት

ሀ. በምርጫ ህጉ መሠረት የምርጫ ቦርድ የሚመሰርተው የፓርቲዎች የጋራ አካል እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለምርጫ ውድድር ተመዝግበው የፖለቲካ ፓርቲዎች ስነምግባር ደንብ ባወጡትና በተፈራረሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይመሰረታል፡፡

ለ. የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል የሆኑ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው ለምክር ቤቱ ከ3-5 አባላት ይወክላሉ፡

### 1.3.2 ክልላዊ አደረጃጀት

ሀ. በክልል ለምርጫ ውድድር በተመዘገቡ ፓርቲዎች ይቋቋማል፣

ለ. በክልል ለምርጫ ከተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ፣ ቋሚ እንደሁኔታው ወደፊት በሚወሰን አባላት ይመሰረታል።

1.3.3 በምርጫ ክልል ደረጃ ያለው አደረጃጀት በምርጫ ክልሉ በሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ይመሰረታል፡፡ ሆኖም የግል ተወዳዳሪዎች በታዛቢነትና ጉዳያቸውን በሚመለከት በአስረጂነት የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

1.3.4. የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ ሲቀረጽ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ያልተሳተፉ ሌሎች ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንቡን ተቀብለው ሲፈርሙ በምክር ቤቱ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሁኔታ በመሥራች ፓርቲዎች ተመክሮበት እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

## 1.4 የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ሚና

1.4.1 በኢትዮጵያ በነፃነት ማሰብና መተግበር፣ በአጠቃላይ ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት የሚጎለብቱበትን ይመክራል፣ የተደረሱባቸውንም ስምምነቶች ይተገብራል፣ አባል ድርጅቶቹ እንዲተገብሩ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣

1.4.2 ምርጫው ግልጽ፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ተአማኒና ሰላማዊ ሆኖ እንዲካሄድ ፓርቲዎች ያለባቸውን ሚና በአግባቡ እንዲወጡ ያደርጋል፣

1.4.3 ፓርቲዎች በልዩ ልዩ የምርጫ ጉዳዮች አፈፃፀም ዙሪያ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ለመወያየትና ችግሮችን ለመፍታት እንዲችሉ መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣

1.4.4 የስነምግባር ደንቡን አስመልክቶ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው ትምህርት መስጠታቸውን ያረጋግጣል፡፡

1.4.5 የስነምግባር ደንቡ በሁሉም ፓርቲዎች ተፈፃሚ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

1.4.6 የስነምግባር ደንቡ በተጣሰ ጊዜ ከሚመለከታቸው ፓርቲዎች የተውጣጣ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም ወይም የማጣራት ኃላፊነቱን ራሱ በመውሰድ ጉዳዩን ያጣራል፣ ይመረምራል፣

1.4.7 ተጣርቶ በተገኘው ውጤት ላይ በመመስረት አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫ ቀይሶ በፓርቲዎቹ የተባበረ ጥረት በተግባር እንዲተረጎም ያደርጋል፡፡ በስነ ምግባር ደንቡና በሌሎች የምርጫ አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ የተደረሰበትን የጋራ ስምምነት የውሳኔ ሃሳብ ለመንግሥትና ለምርጫ ቦርድ ያቀርባል፡፡

1.4.8 ፓርቲዎች በልዩ ልዩ የምርጫ አፈፃፀም እና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት ጉዳዮች ላይ ተገናኝተው እንዲመክሩ ለማድረግ እና የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ የሚያስችል ቋሚ የስብሰባ ጊዜ ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ II. <u>የስነምግባር ደንብ ስለማስተዋወቅ</u>

2.1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ የፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ህጉን ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በማስተማር በአባላቱ መታወቁንና መከበሩን ማረጋገጥ አለበት።

2.2. እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫው ሂደት መራጩን ህዝብ ስለ ስነምግባር ደንቡ ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶች መደገፍና ማስተዋወቅ አለበት፡፡

2.3. ማንኛውም ለምርጫ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ

2.3.1. ህጉን ማክበር

2.3.2. እጩ ተወዳዳሪዎቹ፣ ባለስልጣኖቹ፣ ወኪሎቹ፣ አባሎቹና ደጋፊዎቹ የስነ ምግባር ኮዱንና የምርጫ ህጉን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ

መምራት እና ማክበራቸውንም የሚያረጋግጡ እርምጃዎች መውሰድ አለበት።

2.4. ማንኛውም ለምርጫ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ፤ ሁሉም ሰው

2.4.1. የፖለቲካ እምነቱን እና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፣

2.4.2. በሌሎች የፖለቲካ እምነት እና አስተያየት ላይ የመከራከር እና የመተቸት፣

2.4.3. የራሱን የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶች የማተምና የማሰራጨት፣

2.4.4. ፖስተሮችን፣ ባነሮችንና ቢልቦርዶችን የመስቀል፣

2.4.5. ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውም አይነት ገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል የምርጫ ድጋፍ የማሰባሰብ፣

2.4.6. አባላትን የመመልመል፣

2.4.7. ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፣

2.4.8. በህዝባዊ ስብሰባዎች የመገኘት፣

መብቶች እንዳሉት በይፋ የመግለፅ ግዴታ አለበት።

2.5. ፓርቲዎችና ዕጩዎች የሥነ ምግባር ደንቡና በደንቡም ለመገዛት ያላቸውን ቁርጠኝነት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው።

2.6. የተመዘገቡ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ነፃና ፍትህዊ ምርጫን የሚጐዳ ወይም የሚያጣጥል (undermine) ማንኛውንም ተግባር በይፋ ያወግዛሉ፡፡

2.7. የምርጫ ቦርዱ ሁሉም ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ሚና የሚጫወቱትን መንግሥታዊና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በስነምግባር ደንቡ ላይ አስፈላጊውን ግንዛቤ እንዲይዙ ተገቢውን ሁሉ ማድረግ አለበት።

2.8. በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በስነ ምግባር ደንቡ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ለሚመለከታቸው ሁሉ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡

2.9. ቦርዱ የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡን ለሚመለከተው አካል ሁሉ የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት፡፡

2.10. የመገናኛ ብዙሃን ይህንን የስነ ምግባር ደንብ አስመልክቶ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡

2.11. የስነምግባር ደንቡን ለማስተማር ብቃት ኖሯቸው ግዴታቸውን ለመወጣት የፈረሙ እና ከቦርዱ ፈቃድ የተሠሰጣቸው አካላት በምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ላይ ትምህርት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ III. <u>የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ በተጣሰ ጊዜ የሚቀርብ አቤቱታ ስለሚመረመርበት ሁኔታ</u>

3.1. ለምርጫ አስፈፃሚ አካላት ለማቅረብ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ተጥሷል ብሎ የሚያምን ወገን በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታ ለፖለቲካ ፓርቲዎቹ የጋራ ምክር ቤት እንዲጣራለት ለማቅረብ ይችላል፡፡

3.2. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስነ ምግባር ደንቡ ተጥሷል የሚል አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ ይህንኑ በራሱ ያጣራል ወይም መርምሮና አጣርቶ የሚያቀርብ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

3.3. ስለ አጣሪ ኮሚቴው አደረጃጀትና አሰራር

3.3.1. አደረጃጀት

የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፡-

ሀ. የስነ ምግባር ጥሰትን አስመልክቶ የቀረበን አቤቱታ ሲታዘዝ እየተከታተለ በማጣራት ሪፖርት የሚያቀርብ አጣሪ ኮሚቴ

በየደረጃው ባለ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡

ለ. አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታ አቅራቢና አቤቱታ የቀረበበት የፖለቲካ ፓርቲ የሚሳተፉበትና በሁለቱም ስምምነት የሚመደብ 3ኛ ገለልተኛ አካላት የያዘ ይሆናል፡፡

ሐ. አጣሪ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

### 3.3.2. አሰራር

በዚህ ደንብ የሚቋቋም የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አለመግባባቶች የሚፈቱበት አሠራር እንደሚከተለው ይሆናል።

ሀ. የሚደራጀው አጣሪ ኮሚቴ ስራውን በገለልተኝነት ማከናወን አለበት፡፡ በአጣሪ ኮሚቴው አባላት መካከል ልዩነቶች ቢከሰቱ የብዙሃኑ ሃሳብ የኮሚቴው ሃሳብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሁዳኑም ሃሳብ ራሱን ችሎ ለፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ይቀርባል፡፡

ለ. አጣሪ ኮሚቴው በማጣራቱ ሂደት ያገኘውን መረጃ አጠናቅሮ ለፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ብቻ ያቀርባል፡፡ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መረጃው እንዴት ለህዝብ እንደሚገልፅ ይወስናል፡፡

ሐ. የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ተጠናቆ በቀረበለት ሪፖርት ላይ በመመስረት ለችግሩ አግባብነት ያለው መፍትሄ ይሰጣል፡፡

መ. የስነ ምግባር ደንቡ ጥሰት አጋጥሟል በተባለ ጊዜ አቤቱታ አቅራቢው ፓርቲ አቤቱታ ከቀረበበት ፓርቲ ጋር በመነጋገር ችግሩን በስምምነት ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

ሠ. የተከሰተው አለመግባባት በስምምነት መፈታት ካልቻለ ጉዳዩ ለፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሪፖርት ሊደረግ ይችላል።

ረ. የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አቤቱታ የሚቀበልበትን አሰራር እና አቤቱታው መፍትሄ የሚያገኝበትን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት እንዲታተም ማድረግ አለበት።

ሰ. የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የቀረበለትን ሪፖርት ወይም አቤቱታ መሰረት በማድረግ በቀጥታ በመመርመር ወይም ከላይ በተጠቀሰው መሠረት የሚቋቋም አጣሪ ኮሚቴ በመላክ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት በማድረግ ችግሩን ይፈታል፡፡

ሸ. የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በፖለቲካ ፓርቲዎች ስምምነት ተግባራዊ የሚሆን የማስረጃ አቀባበልና አቀራረብ ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ አሰራሮችን ለማዘጋጀት ይችላል።

ቀ. ሁሉም አቤቱታዎች (ቅሬታዎች) በአፋጣኝ መጣራት ይኖርባቸዋል።

በ. በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመው አካል ለሚመለከታቸው ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ፍትሀዊ የመሰማት እድል መስጠት አለበት፡፡

ተ. የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውሳኔ የሚተላለፈው በጋራ መግባባት በተባበረ ድምፅ ይሆናል፡፡

3.4. የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ተጥሷል የሚል አቤቱታን ተከትሎ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በራሱ ወይም በአጣሪ ኮሚቴው ለሚያካሂደው ምርመራ ፓርቲዎች፣ እጩ ተወዳዳሪዎችና የሚመለከተታቸው የመንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ IV. <u>የስነ ምግባር ደንብ ጥሰቶች</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥፋቶች የስነምግባር ደንብ ጥሰት ተደርገው ይወሰዳሉ

### 4.1. መደለያ ስለመስጠት ወይም ኃይል ወይም ሥልጣን አለአግባብ ስለመጠቀም

| | |
|---|---|
| 4.1.1. | ማንኛውንም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፣ |
| 4.1.2. | በድምጽ አሰጣጡ ወይም በቆጠራው ጣልቃ የገባ ወይም ያወከ |
| 4.1.3. | ኃይል በመጠቀም ወይም መደለያ በመስጠት መራጩ ሕዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ከመስጠት እንዲታቀብ ያደርገ |
| 4.1.4. | የድምጽ መስጫ ጣቢያ በሀይል የተቆጣጠረ ወይም ሕገ-ወጥ መንገድ በመጠቀም ድምጽ ለማግኘት የሞከረ |
| 4.1.5. | ሥልጣኑን መከታ በማድረግ መደለያ ወይም ቅጣት ወይም ሌላ የማስፈራሪያ ዘዴ የተጠቀመ |
| 4.1.6. | ማንኛውንም መደለያ ወይም ኃይል በመጠቀም እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዲወጡ ወይም እንዳይወጡ ያደረገ |
| 4.1.7. | የመንግሥት ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በራሳቸው የግል ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት የስራ ሰዓት እና ኃላፊነታቸውንና ተቋማቸውን በመጠቀም እጩዎችን ማስተዋወቅ ወይም ሌሎች እጩዎች እራሳቸውን በሕጋዊ መንገድ ለማስተዋወቅ ያላቸውን እድል ያደናቀፈ |
| 4.1.8. | የመንግሥት ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ የተጠቀመ |

4.2. ፍርሃት፣ ሁከት መፍጠር እና ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል:-

| | |
|---|---|
| 4.2.1. | ጫና ወይም ተጽዕኖ በመጠቀም ጣልቃ የገባ |
| 4.2.2. | ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዳያሰራጩ ስጋት እና ፍርሀት የፈጠረ |
| 4.2.3. | እንቅስቃሴው የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመራጩን ሕዝብ እቅንስቃሴ ያደናቀፈ ወይም ያወከ |
| 4.2.4. | ሕዝባዊ ቅስቀሳ ወይም ስብሰባ ወይም ውይይት ወይም ትምህርትና ስልጠና እንዳይካሄድ ያደናቀፈ ወይም ሁከት የፈጠረ |
| 4.2.5. | ሕዝብ ድምጽ ሲሰጥ ያወከ ወይም ድምጽ እንዳይሰጥ ችግር የፈጠረ |
| 4.2.6. | የሌሎች ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጎል ወይም እንዲቋረጥ ወይም እንዲበላሽ ወይም እንዲዳከም ያደረገ |
| 4.2.7. | ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፣ የእግር ጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ፣ ያደናቀፈ፣ ወይም እንዳይሳተፍ የከለከለ |
| 4.2.8. | መራጮችን ያበሳጨ ወይም የመምረጥ መብታቸውን ያደናቀፈ |
| 4.2.9. | ለምርጫው ሂደት የምርጫ አስፈፃሚዎችን እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፀጥታና ደህንነት እንዲረጋገጥ እገዛ ያላደረገ ወይም ያወከ |
| 4.2.10. | መራጩ ህዝብ እንዳይመዘገብ ወይም እንዳይመርጥ ያደረገ |
| 4.2.11. | የድምጽ አሰጣጡን ሚስጥራዊነት ያላከበረ ወይም እገዛ ያላደረገ |
| 4.2.12. | የስነ ምግባር ደንቡ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ በማቅረብ ቅሬታ የማሰማት መብቱን ያለአግባብ የተጠቀመ፣ |

4.3. ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ስለማስተላለፍ

| | |
|---|---|
| 4.3.1. | የምርጫ ዘመቻውን ሰላም የሚያናጋ ወይም ግጭት የሚቆሰቁስ ወይም ስም የሚያጠፋ ወይም አመፅ የሚጋብዝ ወይም ስጋት የሚፈጥር ንግግር ያደረገ |
| 43.2. | በይፋም ሆነ በስውር አመፅን የሚቀሰቅስ ወይም የሚያስፈራራ ቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔቶች ወይም ፖስተር ያሰራጨ |
| 4.3.3. | በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት በህዝቡ ላይ የፍርሃት እና የጭንቀት ሁኔታ የፈጠረ |
| 4.3.4. | የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሚስጥራዊ እንደማይሆን የሀሰት መረጃ የሰጠ |

4.4. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ

| | |
|---|---|
| 4.4.1. | ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይመለምልና ጽ/ቤት እንዳይከፍት ያደናቀፈ፣ ባጠቃላይ የማንኛውንም የፖለቲካ ፖርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፣ |
| 4.4.2. | ፓርቲዎች ልሳኖቻቸው፣ የምርጫ ማስታወቂያዎቻቸው፣ በራሪ ጹሁፎቻቸው፣ ፖስተሮቻቸው እንዳይሰራጩ ወይም እንዲበላሹ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፉ ያወከ ወይም የተለጠፉትን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያጠፋ |
| 4.4.3. | የሌሎች የፖለቲካ ፖርቲዎች ምልክቶች ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ |
| 4.4.4. | የሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ |

4.5. ጋዜጠኞችን ወይም ታዛቢዎችን አለመተባበር

| | |
|---|---|
| 4.5.1. | የፕሬስ ነጻነትን የተጋፋ |
| 4.5.2. | በምርጫ ሂደት ጋዜጠኞችን ያዋከበ ወይንም ስራቸውን ያደናቀፈ |

| | |
|---|---|
| 4.5.3. | የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች ያላከበረ ወይም ያልተባበረ |

4.6. የስነ ምግባር ደንቡን አለማስተዋወቅና ህገወጥ ድርጊቶች አለማውገዝ

| | |
|---|---|
| 4.6.1. | አመፅን ወይም ለአመፅ የሚጋብዙ ወይም የህዝብን ሰላም የሚያናጉ ድርጊቶች ያላወገዘ ወይም ተቃውሞ ያላስተማረ |
| 4.6.2. | ለእጩ ተወዳዳሪዎቹ፣ ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹና ለሕዝቡ ስለ ምርጫውና ስለ ሥነ-ምግባሩ ያላስተዋወቀ ወይም ያላስተማረ |
| 4.6.3. | መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹና አባላቱ ይህን የስነምግባር ደንብ እንዳይጥሱ ቁርጠኛ እርምጃ ያልወሰደ ወይም ደጋፊዎቹ የተከለከለ ተግባር ፈጽመው ሲገኙ ያላወገዘ ወይም አግባብነት ያለው እርምጃ ያልወሰደ |
| 4.6.4. | ኃላፊዎች፣ ተወዳዳሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ማንኛውም ሰው በየትኛውም ጊዜ ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልጽ የሚከለክል መመሪያ ያላወጣ |

## ምዕራፍ V. <u>ስለሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች</u>

5.1. በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፡-

5.1.1. ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ስህተቱን እንዲያርም ወይም እንዲያስተካክል ውሳኔ ማስተላለፍ፡፡

5.1.2. ሥነምግባር ደንቡን የጣሰውን የፖለቲካ ፓርቲ ስም እና ተግባር ጠቅሶ ለህዝብ እንዲጋለጥ (Name and shame) ያደርጋል፡፡ ውሳኔውን በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በሌላ አመቺ በሆነ የመገናኛ ብዙሃን ህዝቡ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

5.1.3. ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሔ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ የመፍትሔ እርምጃ ያልረካ አካል ጉዳዩን በምርጫ ህጉና የዚሁ አካል ሆኖ በወጣው የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ መሰረት ለሚመለከታቸው ማቅረብ ይችላል፡፡

5.1.4. ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሔ እርምጃዎች (Remedies) ጉዳት የደረሰበት ወገን በፍትሐ ብሔር ወይም በወንጀል ለመጠየቅ ያለውን መብት ሊያስቀሩ አይችሉም፡፡

5.2. በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

በምዕራፍ V 5.1 የተዘረዘሩና በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የምርጫ ቦርዱ ከላይ በምዕራፍ IV የተዘረዘሩትን የስነ ምግባር ደንቡን ጥሰት በሚያረጋግጥበት ጊዜ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንደሁኔታው ሊወስድ ይችላል፡፡

5.2.1. ጥፋቱን ለፈፀመው ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

5.2.2. ጥፋቱን የፈፀመ እጩ ወይም ፓርቲ ለአጭር ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ በሕዝብ (public) መገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም ማድረግ፣

5.2.3. ጥፋቱን የፈፀመ ፓርቲ በመንግስት ከሚሰጠው የፓርቲ ፋይናንስ ድጎማ ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ፣

5.2.4. ማንኛውንም በፓርቲ ወይም በግል የቀረበ እጩን እንደ ጥፋቱ ክብደት አይቶ ከምርጫ ተወዳዳሪነት መሰረዝ፣

5.2.5. የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫ ውድድር እንዳይሳተፍ ማገድ፣

5.2.6. ከላይ የተጠቀሰው ማንኛውም እርምጃ ከዚህ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ቅጣቶች ወይም ክልከላዎች ጋር በተደራቢነት የሚወሰድ ሊሆን ይችላል፡፡

5.3. በፍርድ ቤት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

5.3.1. በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ በድምፅ መስጫ እለት ድምፅ ከመስጠት ውጭ በሌላ ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ በድምፅ መስጫ ጣቢያ አካባቢ መሳተፍ ወይም በተከለከለው ጊዜ ውስጥ የምርጫ ውጤትን ማተም፣ ማባዛት፣ ወይም በምዕራፍ IV 4.1፣ 4.2፣ 4.3 እንደሚከተለው

የተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈፀም በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል።

ሀ/ በምርጫ ቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ጣልቃ የገባ፣ መደለያ ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት አንድ ሰው ተግባሩን እንዳያከናውን ያደረገ፣

ለ/ ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት (out come) ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን (hostility) ወይም ፍርሀትን የሚያሰፍን ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ ያሳተመ፣

ሐ/ የምርጫ ሚስጥራዊነትን የጣሰ፣

መ/ ከድምፅ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን የተላለፈ፣

ሠ/ የምርጫ ቦርዱን እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንቅስቃሴ ያወከ፡፡

5.3.2. የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለፅ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎች መብት ወይም ማስመሰል አስመልክቶ ክልከላዎች የሚጥሱ ድንጋጌዎች የማያከብር ወይም ሐሰት መሆኑን እያወቀ ወይም እውነት ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ንግግር የሚያደርግ ሰው በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

5.3.3. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ሆንብሎ የምርጫ ቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈፃሚው፣ የምርጫ ቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩን

ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት የሆነ ወይም ያደናቀፈ እንደሆነ፤

ለ/ የምርጫ ቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ያቋረጠ ወይም በነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤

ሐ/ ሆን ብሎ በምርጫ ቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውም ተግባር የፈፀመ፣

መ/ ከላይ በምዕራፍ IV 4.4 እና 4.5 የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ እንደሆነ፤

በገንዘብ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡